# ዝቅ ባለ ዋጋ የጤና እንክብካቤን ለማግኘት ወይም የጤና መድህን ለማግኘት የሚረዱ ግልጋሎቶች

## በዝቅተኛ ዋጋ የጤና እንክብካቤ ይፈልጉ

- **ወደጥቅማ ጥቅሞች የሚያገናኙ፤ MN ዝቅተኛ ወጪ የጤና እንክብካቤ ማውጫ**
  (www.bridgetobenefits.org/MN_Low_Cost_Health_Care_Directory)
  በቅርብዎ በአነስተኛ ዋጋ የሚያክሙ ክሊኒኮችን ዝርዝር ለማግኘት ካውንቲዎን ያስገቡ።

- **የሚኒሶታ የህብረተሰብ ጤና ማህበር ማእከሎች (MNACHC)**
  (https://mnachc.org/community-health-centers/find-a-health-center/)
  በአቅራቢያዎ የሚገኘውን የማህበረሰብ ጤና ማእከል (በፌዴራል ብቃት ደረጃ ያለፈ የጤና ማእከል) ለማግኘት ካርታውን ይጠቀሙ ወይም የአከባቢዎን አድራሻ ያስገቡ። የማኅበረሰብ ጤና ማእከሎች እንክብካቤ የማግኘት ዕድላቸው ውስን ለሆነ ሰዎች የሕክምና፣ የጥርስ እና የባህሪ የጤና አገልግሎቶችን ይሰጣሉ።

## የጤና መድህን ያግኙ

- **MNsure ለ ኢንሹራንስ ያመልክቱ እና ይመዝገቡ**
  (www.mnsure.org/new-customers/apply/index.jsp)
  እንደ Medical Assistance (ሜዲካል አሲስታንስ) እና MinnesotaCare (ሚኔሶታኬር) ላሉ መድህኖች በኢንተርኔት ማመልከት ይችላሉ ወይም የምዝገባ ባለሙያ ሊረዳዎት ይችላል። በ MNsure የተመዘገቡት አብዛኞቹ የሚነሶታ ነዋሪዎች የገንዘብ ድጋፍ የማግኘት ብቃት አላቸው።

- **MNsure አስተናጋጆች**
  (https://www.mnsure.org/help/find-assister/find-navigator.jsp)
  Medical Assistance እና Minnesota Care እንክብካቤ ለመመዝገብ (ብቁ ከሆኑ) አስተናጋጆች ሊረዱዎት ይችላሉ። እንዲሁም በግል የመድህን ዋስትና ውስጥ እንዲመዘገቡ እና መሰረታዊ የጤና የመድህን ሽፋን ትምህርት እንዲያገኙም ሊረዱዎት ይችላሉ። ብዙዎቹ አስተናጋጆች በማኅበረሰብ ድርጅቶች ውስጥ የሚገኙ ሲሆን ቻይንኛ፣ ሶማሊኛ፣ ስፓኒሽ፣ ሞንግ እና ቬትናምኛን ጨምሮ በቋንቋዎች ድጋፍ ይሰጣሉ።

- **የሆስፒታል ብቁነት ግምት መርሃግብር**
  (https://mn.gov/dhs/partners-and-providers/policies-procedures/minnesota-health-care-programs/provider/hpe/)
  በሆስፒታል በሚቆዩበት ጊዜ ለ Medical Assistance ወይም ለ Minnesota Care ለመመዝገብ ይችሉ ይሆናል። መስፈርቶቹን የሚያሟሉ ከሆነ፣ የተሟላ ማመልከቻ ከመሙላትዎ በፊት ለአገልግሎቶች ሽፋን ልያገኙ ይችላሉ።

## ተጨማሪ የጤና አገልግሎቶችን ያግኙ

- **የአካባቢ የጤና መምሪያዎች እና የማህበረሰብ ጤና ቦርዶች**
  (https://www.health.state.mn.us/communities/practice/connect/findlph.html)
  መመሪያ ለማግኘት እና ብቁ ሊሆኑ ስለሚችሏቸው አገልግሎቶች መጠየቅ ከፈለጉ በአከባቢዎ የሚገኘውን የጤና ጥበቃ መምሪያ እና/ወይም በካውንቲዎ የሚገኘውን የህብረተሰብ የጤና ቦርድ ያነጋግሩ።

Minnesota Department of Health
625 Robert St. N., PO Box 64975
St. Paul, MN 55164-0975
651-201-5414
www.health.state.mn.us

02/13/2020

*ይህንን መረጃ በተለየ ሁኔታ ለማግኘት ይደውሉ፤ 651-201-5414*